


**በፕሬዘደንት ዲየተር ኤፍ. ኡክዶርፍ**
*የቀዳሚ አመራር ሁለተኛ አማካሪ*

# ሁሉም መልካም ነው

ስለ መስራቾቻችን ውርስ ሳስብ፣ በጣም ስሜት ከሚነኩ ነገሮች ወደ አይምሮዬ የሚመጣው "ኑ ኑ ቅዱሳን" የሚለው መዝሙር ነው (*መዝሙር*፣ ቁጥር 30)። እነዚያ ወደ ሶልት ሌክ ሸለቆ ረጅሙን አድካሚ ጉዞ በሚያደርጉበት ወቅት በብዛት ይህንን መዝሙር ዘምረው ነበር።

ለእነዚህ ቅዱሳን ሁሉም መልካም እንዳልነበረ በደምብ አውቃለሁ። እነርሱ በህመም፣ ሙቀት፣ ድካም፣ ቅዝቃዜ፣ ፍርሀት፣ ረሀብ፣ ህመም፣ ጥርጣሬ፣ እናም ደሞ በሞትም ተጠቅተው ነበር።

"ሁሉም መልካም አይደለም" ብሎ ለመጮህ በቂ ምክንያት ቢኖራቸውም፣ ግን ዛሬ እኛ ከማድነቅ ዉጪ ምንም ማድረግ የማንችላቸውን ባህሪ እነርሱ አዳበሩ። እነርሱ ከችግሮቻቸው በላይ ወደ ዘለአለማዊ በረከቶች ተመለከቱ። በሁኔታዎቻቸው ውስጥ አመስጋኝ ነበሩ። ለተቃራኒው ምክኒያት ቢኖርም እንኳ፣ እነርሱ "ሁሉም መልካም ነው" ሲሉ በሙሉ በነበራቸው እርግጠኝነት ዘመሩ።

በእኛ ክፍል የውስጥ ነፀብራቅን ካላመጣ በቀር ለመስራቾች ያለን ሙገሳ ባዶ ነው። መስዋእታቸውን እና መሰጠታቸውን ሳሰላስል የሚያነሳሱኝን የእነርሱን ጥቂት ባህሪያት ልጥቀስ።

**ርህራሄ**

መስራቾች የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የፖለቲካ የኋላ አመጣጥን ከግምት ሳያስገቡ እርስ በእርስ ይንከባከቡ ነበር። ግስጋሴአቸውን ቢያዘገየውም፣ እንቅፋት ቢፈጥርም፣ ወይም የግል መስዋእት እና ልፋት ቢያስከትልም፣ እነርሱ እርስ በእርስ ይረዳዱ ነበር።

ግብ ተኮር እና ተከታይ በሆነው አለማችን ውስጥ፣ የግል ወይም የቡድን አላማዎች ሌሎችን ከመንከባከብ ወይም የእግዚአብሔርን መንግስት ከመገንባት በላይ ቅድሚያ ሊወስዱ ይችላሉ። በዛሬው ማህበረሰብ ውስጥ ፣ የተወሰነ የአመለካከት ግብ ላይ መድረስ የብቁነት መለኪያ ሊመስል ይችላል።

ግብን ማቀድ እና ማሳካት ድንቅ ነገር ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ግብን ላይ የመድረስ ስኬት ሌሎችን በመናቅ፣ ጣል ጣል በማድረግ፣ ወይም በመጉዳት ከመጣ፣ ያ ስኬት የሚያስከፍለው ዋጋ በጣም ውድ ይሆናል።

መስራቾቹ አብረዋቸው የነበሩትን ጠብቀዋል፣ ነገር ግን በተጨማሪም ለሚከተሏቸው ጋሪዎች እህል በመትከል፣ ከእነርሱ በኋላ ስለሚመጡትም አስበዋል።

የቤተሰቦች እና የጓደኞችን ጥንካሬ ያውቁ ነበር። እርስ በእርስ በመደጋገፋችው ምክንያት፣ ጠንካራ ሆኑ። ጓደኞች ቤተሰብ ሆኑ።

ከፈተና እራሳችንን በመነጠል እና በምትኩ፣ እርስ በእርስ መረዳዳት እና የእርስ በእርስ ርህራሄ እና ፍቅር ሊኖረን እንደሚገባ መስራቾች እንደ ጥሩ ማስታወሻ ያገለግላሉ።

**ስራ**

"ኑ፣ ኑ ቅዱሳን፣ መከራን ወይም ስራን አትፍሩ።"

ይሄ ሀረግ ለደከሙ ተጓዦች እንደ መሪ መዝሙር ሆነ። እነዚህ ታላቅ ነብሳት ምን ያህል ከባድ ስራ እንደሰሩ ለመገመት ይከብዳል። ካደረጓቸው ቀላል ነገሮች መካከል አንዱ የእርምጃ ጉዞ ነው። ምግብ ለማዘጋጀት፣ ሰረገላዎችን ለመጠገን፣ እንስሳዎችን ለመጠበቅ፣ የታመሙትን እና የደከሙትን ለማገልገል፣ ውሀ ለመፈለግ እና ለመቅዳት፣ እና እየጨመሩ ከሚመጡት አደጋዎች እና የምድረ በዳ አስፈሪ ነገሮች እራሳቸውን ለመጠበቅ ሁሉም በአንድነት መስራት ነበረባቸው።

እግዚአብሔርን እና ህዝቡን ለማገልገል እና ወደ ሶልት ሌክ ሸለቆ ለመድረስ በግልጽ በሚተረጎሙ አላማዎች እና ግቦች ነበር በእያንዳንዱ ጠዋት የነቁት ። በእያንዳንዱ ቀን እነዚያ አላማዎች እና ግቦች ለእነርሱ ግልጽ ነበሩ፤ ማድረግ የነበረባቸውን ያውቁ ነበር እና የእያንዳንዷ ቀን እድገት ትርጉም ነበረው።

በእኛ ጊዜ—አብዛኛው ፍላጎታችን በእኛ አቅራቢያ ሆኖ— ከፊት ያለው መንገድ ትንሽ የሚያንገጫግጭ ሲሆን ወይም ዳገቱ በእኛ ላይ ከፍ ያለ ሲመስል ወደ ጎን ለመዞር ወይም ተስፋ ለመቁረጥ እንፈተናለን። በእነዚያ ጊዜያት፣ በሽታ፣ ችግር፣ ህመም፣ እና ሞትም ቢሆን ከመረጡት መንገድ እንዲለያቸው ስላልፈቀዱት እነዚያ ወንዶች፣ ሴቶች፣ እና ህጻናትን እንድናስብ ሊያነሳሳን ይችላል።

ከባድ ነገሮችን ማድረግ አካል፣ አእምሮ፣ እና መንፈስን ትልቅ እና ጠንካራ እንደሚያደርግ፤ የእነርሱን መለኮታዊ ተፈጥሮ መረዳት

እንደሚያጎላ፤ እና ለሌሎች ያላቸውን ርህራሄ ከፍ እንደሚያደርገው መስራቾች ተምረው ነበር። ይሄ ልምድ ነብሳቸውን አጸናው እናም ከአድካሚው የሜዳ እና ተራራ ጉዞአቸው በኋላ ቆይቶም በረከት ሆነላቸው።

***ተስፈኝነት***

*መስራቾች ሲዘምሩ፣ “ነገር ግን በደስታ ተጓዙ” ብለው ሶስተኛ ትምህርትን ዘመሩ።*

በብዙ ብንባረክም ግን በጣም ያለ ደስታ ለመሆን መቻላችን የዘመናችን አንዱ ታላቅ ምጸት ነው። አስገራሚ ብልጽግና እና ቴክኖሎጂ ያስደምመናል እና በጥበቃ፣ መዝናኛ፣ ፈጣን መሳካት፣ እና በምቾት ያጥበናል። እና ግን በዙሪያችን ሁሉ ደስታ ማጣትን እንመለከታልን።

ብዙ መስዋእት የከፈሉት መስራቾች፣ በረሀብ እና ለመኖር በጣም መሰረታዊ ነገሮችን በማጣጥ ኖሩ። በእድል ወይም በድንገት ደስታ እንደማይመጣ ተረድተው ነበር። በእርግጥም ይህ ምኞታችን ሁሉ እውን በመሆኑም አይመጣም። ደስታ በውጫዊ ሁኔታዎች አይመጣም። ምንም ነገር በዙሪያችን እየተከሰተ ቢሆንም እናኳ፣ ደስታ የሚመጣው ከውስጥ ነው።

መስራቾች ያንን አውቀው ነበረ፣ እና በዚያ መንፈስ በሁሉም ሁኔታዎች እና በማንኛውም ፈተና፣ እንዲሁም በእነዚያ የነብሳቸውን ጥልቅ ውህ ድረስ ደርሰው በበጠበጡአቸው ፈተናዎች ውስጥ ደስታን አገኙ።

***ፈተና***

አንዳንድ ጊዜ መስራቾች ያሳለፉትን መለስ ብለን እንመለከት እና ኡፈይ ብለን፣ “ተመስገን በዚያ ጊዜ ባለመኖሬ” እንላለን። ነገር ግን ዛሬ እኛን ማየት ችለው ቢሆን፣ እነዚያ ብርቱ መስራቾች ተመሳሳይ የምስጋት ድምጽ አይኖራቸው ይሆን ብዬ እገረማለሁ።

ጊዜ እና ሁኔታዎች ቢቀየሩም፣ ፈተናዎችን የመጋፈጥ እና በእግዚአብሔር ስር እንደ አሳቢ እና የበለጸገ ማህበረሰብ በስኬት የመኖር መሰረተ ሀሳቦች አልተቀየሩም።

እምነት እንዲኖረን እና በእግዚአብሔር መታመንን ከመስራቾች መማር እንችላለን። ለሌሎች ርህራሄ እንዲኖረን መማር እንችላለን። ስራ እና ትጋት ለጊዜአዊ ብቻ ሳይሆን ግን በመንፈሳዊም እንደሚባርኩን መማር እንችላለን። ምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ብንሆንም ደስታ እንዳለ መማር እንችላለን።

መስራቾችን ማክበር እና ምስጋናችንን ማሳየት የምንችለው ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ታማኝነትን፣ ለሰው ሁሉ ርህራሄ እና ፍቅር፣ እና ትጉነትን፣ ቀናነትን፣ እና መስራቾች በራሳቸው ህይወት ያሳዩትን ደስታ በራሳችን ህይወት ውስጥ ስናጠቃልል ነው።

ያንን ስናደርግ፣ አስርተ አመታትን አልፈን እየሄድን፣ የእነዚያን ድንቅ የመስራቾች እጅ በእጃችን በመውሰድ፣ እና “ሁሉም መልካም ነው! ሁሉም መልካም ነው!” ብለን በመዘመር ድምጻችንን በእነርሱ ድምጽ ላይ ለመጨመር እንችላለን።

በ© 2015 Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/15 (እ.አ.አ). ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/15 (እ.አ.አ).
*First Presidency Message, July 2015*. Amharic. 12587 506 ትርጉም

**ከዚህ መልእክት ማስተማር**

ከምትጎበኙአቸው ጋር “ኑ፣ ኑ ቅዱሳን” የሚለውን በመዘመር ለመጀመር ትፈልጉ ይሆናል (*መዝሙር፣* ቁጥር 30)። የርህራሄ፣ የስራ እና የተስፈኝነትን መርሆዎች እናንተ ወይም የምታውቁት ሰው ሲከተል የነበረውን ተሞክሮ ማካፈል ትችላላችሁ። ከተነሳሳችሁ፣ እነዚህን መርሆዎች በመከተል የሚመጡትን በረከቶች መመስከር እና ተመሳሳይ በረከቶችን ለምትጎበኟቸው ቃል ልትገቡ ትችላላችሁ።

## ወጣቶች

### መዝገብን መጠበቅ

ፕሬዘዳንት ኡክዶርፍ የእኛን ጊዜ ከመስራቾች ጋር ያነጻጽራሉ። ሜዳዎችን ባታቋርጡም እንኳ፣ ከምታስቡት በላይ እናንተ ልክ እንደ መስራቾቹ ናችሁ! ርህራሄ፣ ጠንካራ ስራ እና ተስፈኝነትን እናንተም ማሳየት ትችላላችሁ። በጠበቋቸው መዛግብት ይህንን ባህሪያት እንዳሳዩ እንዳወቅነው ሁሉ፣ በእናንተ የግል መዝገብ ትውልዳችሁ እናንተን ሊያውቁ ይችላሉ።

በግል መዝገባችሁ ስለራሳችሁ ጥቂት ለመመዝገብ የተወሰኑ ደቂቃዎችን ውሰዱ። እንዴት ምስክርነታችሁን እንዳገኛችሁ ወይም በሰማይ አባት እርዳታ እንዴት ችግሮችን እንዳሸነፋችሁ መንፈሳዊ ነገሮችን መጻፍ ትችላላችሁ። (አንድ ቀን መዝገባችሁን ሊያነቡ የሚችሉትን) የቅድመ ልጅ ልጆቻችሁን የየቀን ህይወታችሁ ምን የመስል እንደነበር በማሳወቅ ልትረዱም ትችላላችሁ። በትምህርት ቤት ምን የትምህርት ጥናቶችን እየሰራችሁ ናችሁ? ክፍላችሁ ምን ይመስላል? ከቤተሰባችሁ የምትወዱት ትውስታ ምንድን ነው?

በየቀኑ ጥቂት መጻፍ ስትጀምሩ፣ ልክ መስራቾቹን እንደመራቸው፣ እንዴት የሰማይ አባት በየቀን ህይወታችሁ እንደሚረዳችሁ የተጠራ እይታ ሊኖራችሁ ይችላል፣ ያም ብቻ ሳይሆን ለራሳችሁ የወደፊት ዘር ቅርስ ትተዋላችሁ።

## ልጆች

### የመስራቾቹን ምሳሌ መከተል

ፕሬዘዳንት ኡክዶርፍ መስራቾች ለሰማይ አባት ፍቅርን ያሳዩበትን ጥቂት መንገዶች አካፈሉ። የእነርሱን ምሳሌ መከተል ትችላላችሁ። እንዲያስጀምራችሁ ጥቂት ሀሳቦች እነዚህ ናቸው፤

**ርህራሄ**

☐ ለአዘነ ሰው ደግ ጽሁፍን ጻፉ ወይም አንድ መልካም ነገር አድርጉ።

☐ ለአንድ የክፍላችሁ ጓደኛ በቤት ስራው ወይም ስራዋ አግዙ።

**ስራ**

☐ ግብን አቅዱ። በዚህ ወር ግባችሁን ለማሳካት እንዲረዳችሁ በየቀኑ አንድ ነገር አድርጉ።

☐ ወላጆቻችሁን እራት በማዘጋጀት አግዙ።

**ተስፈኝነት**

☐ በህይወታችሁ 10 የደስታ ነገሮችን ዘርዝሩ።

☐ ለምታዩት ሰው በሙሉ ፈገግ በሉ።

# የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ባህሪያት፤ ይቅር ባይ እና መሀሪ

እምነት፣ ቤተሰብ፣ እርዳታ

*በጸሎት መንፈስ ይህንን መረጃ አንብቡት እና ምን እንደምታካፍሉ ለማወቅ እሹ። የአዳኝን ህይወት እና ተልኮውን መረዳት በእርሱ ያላችሁን እምነት የሚያሳድገው እና በሴቶች የቤት ለቤት ትምህርት ምክንያት የምትንከባከቧቸውን የሚባርከው እንዴት ነው? ለተጨማሪ መረጃ ወደ www.reliefsociety.lds.org።*

*ተከታታይ በሆነው የቤት ለቤት መልእክት ይሄ የአዳኝን ባህሪያት የያዘው ክፍል ነው።*

ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር ሲል እና ለእኛ ምህርት ሲያደርግ እንደነበር መረዳት እኛ ሌሎችን ይቅር እንድንል እና ምህረት እንድናደርግ ሊረዳን ይችላል። “ኢየሱስ ክርስቶስ አርአያችን ነው፣” ብለዋል ፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ. ሞንሰን። “ህይወቱ የፍቅር ውርስ ነበር። በሽተኛዎችን ፈወሰ፣ የተጨቆኑትን ከፍ አደረገ፣ ሀጢያተኛን አዳነ። በመጨረሻ የተናደዱት ወንበዴዎች ሕይወቱን ወሰዱት። ይሁን እንጂ በጎለጎታ ኮረብታ ላይ— በሟችነት ውስጥ የርህራሄና የፍቅር ታላቅ ውጤታማ አገላለፅ የሆኑት— እነዚህ ቃላቶች ያስተጋባሉ፥ ‘አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁትምና፤ ይቅር በላቸው’ ”።[1]

የሌሎችን መተላለፍ ይቅር ካልን፣ የሰማይ አባታችን ደግሞ እኛን ይቅር ይለናል። ኢየሱስ እንዲህ ይጠይቆናል “አባታችሁ ሩህሩህ እንደሆነ፣ እናንተም ሩህሮዎች ሁኑ” (ሉቃስ 6፥36) በቀዳሚ አመራር ሁለተኛ አማካሪ የሆኑት ፕሬዘደንት ዲይተር ኤፍ. ኡክዶርፍ እንዲህ ብለዋል፣ “ለእኛሀጢያት ይቅርታ የሚመጣው ከሁኔታዎች አንጻር ነው።” “ንስሀ መግባት አለብን። . . . ሁላችንም በአንድ ወቅትም ሆነ በሌላ፣ በየዋህነት ወደ ምህረት ወንበር ቀርበን እና ለጸጋ አልማለድንም? ለሰራናቸው ስህተቶች እና ለፈጸምናቸው ሀጢያቶች ይቅር ለመባል በሙሉ የነብሳችን ጉልበት ምህረትን አልተመኘንምን? . . . የክርስቶስ የሀጢያት ክፍያ ልባችሁን እንዲለውጥ እና እንዲፈውስ ፍቀዱ። እርስ በእርስ ተዋደዱ አንዱ ለሌላው ይቅር ይበል።”[2]

### ተጨማሪ ቅዱስ መጻህፍቶች

ማቴዎስ 6፥14–15፤ ሉቃስ 6፥36–37፤ አልማ 34፥14–16

### ከቅዱሳት መጻህፍት

የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት አባል ሽማግሌ ጄፍሪ አር. ሆላንድ እንዲህ አሉ፣ “እኛ ይቅር እንደተባልነው ይቅር ማለት አለብን”።[3] የአባካኙ ልጅ ታሪክ የይቅርታን ሁለቱንም ጎኖች ያሳየናል፥ አንዱ ልጅ ይቅር ተብሏል እና ሌላው ልጅ ይቅር ለማለት ይታገላል።

ታናሹ ልጅ ውርሱን ወሰደ፣ በፍጥነት አጠፋው፣ እና ርሀብ ሲመጣ፣ አሳማ የመመገብ ስራን ሰራ። ቅዱስ መጽሀፍት እንደሚሉት “ወደ ልቡ ሲመለስ፣” ወደ ቤት ተመለሰ እና ልጁ ለመሆን ብቁ እንዳልሆነ ለአባቱ ተናገረ። ነገር ግን አባቱ ይቅር አለው እና ለበአልም ፍሪዳ አረደለት። ታላቁ ልጅ ከእርሻ ስራው ተመለሰ እና ተናደደ። ለብዙ አመታት እንዳገለገለ፣ ትእዛዙንም ከቶ እንዳልተላለፈ፣ ግን “ደስ እንዲለኝ አንድ ጠቦት እንኳ አልሰጠኸኝም” በማለት አባቱ እንዲያስታውስ አደረገ። አባቱ መልሶ፣ “ልጄ ሆይ፣ አንተ ሁል ጊዜ ከእኔ ጋር ነህ፣ ለእኔም የሆነ ሁሉ ያንተ ነው። ዳሩ ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበር፣ ህያው ስለሆነ፣ ጠፍቶም ነበር ስለተገኘ ደስ እንዲለን ፍሥሀም እንድናደርግ ይገባናል” (ሉቃስ 15፥11–32 ተመልከቱ)።

ማስታወሻዎች

1. ቶማስ ኤስ፣ ሞንሰን፣ “Love, the Essence of the Gospel፣” *Liahona,* ግንቦት 2014 (እ.አ.አ)፣ 91።
2. ዲይተር ኤፍ፣ ኡክዶርፍ፣ “The Merciful Obtain Mercy፣” *Liahona,* ግንቦት 2012 (እ.አ.አ)፣ 70፣ 75፣ 77፤ በመጀመሪያው ላይ ትኩረት ተሰጥታል።
3. ጄፍሪ አር. ሆላንድ፣ “The Peaceable Things of the Kingdom፣” *Ensign,* ህዳር 1996 (እ.አ.አ)፣ 83።

### ይህን አስቡበት

ይቅር ማለት ይቅር ባዩን እንዴት ይጠቅማል?

በ© 2015 Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/15 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/15 (እ.አ.አ) *Visiting Teaching Message, July 2015.* Amharic. 12587 506 ትርጉም